**የፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም "የጓል መቀሌ" እና "የለማኙ ቁስ" ኑሮ እንደ ማስረጃ**

**ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ)**

ወቅቱ እንደ የዜና አቀነባበሪዎች ሁሉ እኛ ተቺዎችም ጭምር ሁኔታዎች በየሰከንዱ እየተቀያየሩ በመጡ ቁጥር በየቀኑ እንድንተችባቸው ተገድደናል። በዚህ ቅርብ ጊዜ ተከታትሎ እየታየ ያለው ውጥረት የሁላችንም ቀልብ ስቧል።የተለያዩ ሰዎች የተለያዩ ትችቶች እየሰጡ ነው። በተለይም ወሎ ውስጥ እየታየ ያለው ሁኔታ እና በትግራይ "ኣልትራ ናሺናሊስት" (ፋሺስት) ምሁራን እና የነሱን ዘመቻ በሚያስተጋቡ የዜና አውታሮች በኩል እየተሰነዘረ ያለው የትግራይ ሕዝብ የመገንጠል ሁኔታን አስመልከቶ ብዙ ተቺዎች እንደ የፖለቲካ ምጥቀታቸው የተሳሳተም፤ያልተሳሳተም፤ግምታዊም፤ትንቢታዊም የሆኑ አስተያየቶች እየሰነዘሩ ነው። ከነዚህ ውስጥ ዛሬ ያነበብኩት የፕሮፉሰር መስፍን አስተያየት ነው። ፕሮፌሰር መስፍን ያለውን በጥቅስ ላስቀምጥ፡-

*<<ወያኔ ትግራይን ከተቆጣጠረ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ የትግራይ ሕዝብ በአጠቃላይ ያገኘውን ጥቅምና የኑሮ መሻሻል — እያንዳንዱ አባወራ ራሱንና ቤተሰቡን በየዕለቱ በተሻለ ሁኔታ መመገብ፣ ማልበስ፣ የተሻለ መኖሪያ ቤት፣ የተሻለ የጤና አጠባበቅና ትምህርት … አግኝቷል ወይ?>>(መስፍን ወ/ማርያም የወቅቱ ትንተና ጽሁፍ የተገኘ)*

የመሳሰሉ በርካታ ሃያሲያን የተቻላቸውን ያህል ሰንዝረዋል።

በፕሮፌሰር መስፍን ብጀምር፡-

*<<ወያኔ ትግራይን ከተቆጣጠረ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ የትግራይ ሕዝብ በአጠቃላይ ያገኘውን ጥቅምና የኑሮ መሻሻል — እያንዳንዱ አባወራ ራሱንና ቤተሰቡን በየዕለቱ በተሻለ ሁኔታ መመገብ፣ ማልበስ፣ የተሻለ መኖሪያ ቤት፣ የተሻለ የጤና አጠባበቅና ትምህርት … አግኝቷል ወይ?>>* የሚለው የፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያምም ሆነ መሰል አቋዋም ያላቸው ተከራካሪዎች ለጆሮአችን አዲስ አይደለም። ይህ የወቅቱ ትንተና ለረዢም አመታት የተባለ ቢሆንም፤ ለ27 አመት የሰለቸን ግን ምንም ማስረጃ የሌላቸው ተከራካሪዎች መሆናቸውን አይተናል። አስፕሪን እና ፋሻ ለማግኘት ሲቸግር የነበረ በረሃብ ሲገረፍ የነበረው የትግራይ ሕዝብ ወያኔ ወደ ስልጣን ከወጣ ወዲህ በክ/ሃገሩ የታየው ዕድገትና መሰረታዊ ተቋሞች (ፋብሪካዎች፤ መኪና የሚሰሩ ኢንዳስትሪዎች፤የትምህርት ተቋማትና የጤና ተቋማትና አዋላጆች፤በልዩ መስክ የተካኑ ሃኪሞች፤የሕክምና (የልብ ጥገና መሳሪያዎችና ስፔሺያሊስትስ...) ከገጠሩ ሕዝብ ርቀትና ቅርበት፤ የተማረ የሰው ሃይል፤ የደን ጥበቃ፤መስኖ፤መጓጓዣ....) ለብዙ አመታት ማስረጃቸውን ለማሳየት ብንሞክርም፡- የተሻለ ጤና፤የተሻለ ትምህርት አላገኘም

ይላሉ። ለምሳሌ ፕሮፌሰሩ "የተሻለ ጤና፤የተሻለ ትምህርት አላገኘም" ብለው በድፍን ከመከራከር ባሻገር፤ ትግሬዎች በድህንት እየማቀቁ ለመሆናቸው የሚሰጠን መከራከሪያው ካንድ እንደሳቸው ያለው ምሁር የማይጠበቅ የሚከተለው ማስረጃ ይሰጡናል።

<<ትግሬዎች በወያኔ አገዛዝ ተጠቅመዋል የሚባለውን ወሬ በአሜሪካም ሆነ በአውሮፓ፣ በኢትዮጵያም ስቃወም ብዙ ዓመታት ሆኖኛል፤አሁንም እቃወመዋለሁ፤ በየቀኑ የሚያጋጥሙኝ ያፈጠጡ እውነቶች ከጅምላ ወሬው ጋር አይሄዱልኝም፤ አንድ ጓደኛዬ ጫማውን ሲያስጠርግ አጠገቡ ቆሜ እያወራን ሳለ አንድ ቄስ የዕለት ምግባቸውን ለመኑ፤ የችጋርን ምንጭና መንገድ ለማወቅ ሁልጊዜ ለማኞችን ከየት እንደመጡ እጠይቃለሁ፤ ቄሱን ስጠይቃቸው ከአሩሲ ነኝ አሉኝ፤ ተቆጣሁና ለምን ይዋሻሉ! ብዬ ሳፈጥባቸው፣ ምን ላድርግ ትግሬ መሆኔን ስናገር ከስድብ ሌላ ሰላይ ነህ እባላለሁ፤ አሉኝ፤ አራት ልጆቿን ይዛ የምትለምን፣ ከኔ ጋር ተዛምደን ‹እጓል መቀሌ› የምላት ሴት አለች፤ ሌሎች ብዙዎችን መጨመር እችላለሁ፤ እንዲያውም በችግር የሚኖሩ ተጋዳላይ ወያኔዎችንም አውቃለሁ፤ እነዚህ በወያኔ አገዛዝ የተጎዱ እንጂ የተጠቀሙ አይደሉም፤የተጠቀሙ አሉ፤ ግን ለአንድ የተጠቀመ ትግሬ ቢያንስ አንድ ሺህ ያልተጠቀሙ ይኖራሉ ብዬ እገምታለሁ፡፡>>

አንድ አካባቢ ድሃን ከሃብታሙ ለመለየት የሚያስችሉ መለኪያዎች አሉ። ምንድ ናቸው፡-"An area is poor when it presents (part of) the following conditions: poor physical resources, lack of physical infrastructure, of trained manpower and of basic services and facilities, inequitable land tenure conditions, production levels below potentials,>> ይላሉ የምጣኔ ሃብት ተመራማሪዎች። አንድ አካባቢ ድሃ የሚያሰብለው የሚከተሉት መሰረታዊ ነገሮች ከሌሉት (ከሞላ ጎደል) ድሃ ይባላል፡- ይህም የአካባቢ የሃብት ምንጭ፤ትምህርት እና የሰለጠ የሰው ሃይል፤ አገልግሎት የሚሰጡ ሕዝባዊ ተቋማት፤የመሬት ይዞታ፤የምርት ግኝትና ውጤቶች......ያለመሟላት የመሳሰሉ ናቸው ይላሉ።

እንግዲህ ከላይ ባጭሩ እንደተቀስኩት እና ብዙ ጌዜ በዝርዝር በመጽሐፍም መልክ የተሰነዱ (ምፅአተ አማራ (ሞረሽ ወገኔ የአማራ ሲቪክ ድርጅት መጽሐፍ የታተመ) የሚለው እና The Pillage of Ethiopia by Eritreans and their Tigrean Sorogates (Dr.Assefa Negash)> እና በኔው የተለያዩት መጽሐፍቶቼ የተዘገቡ የመሳሰሉ መጽሐፍቶች በማስረጃ ቀርበዋል።
ትምህርት ላንድ ማሕበረሰብ ወሳኝ መሆኑን እናውቃለን። በዚህ መልክ ባጭሩ (ወደ ሌሎች ዝርዝር ሳልገባ) የሚከተለውን እንመልከት።በሌላ በኩል የትግራይ መንግሥት መረጃ እንደሚለው እኤአ እስከ 2006 ባሉት (ማለትም ወያኔ ሥልጣን ከጨበጠ 1991 እስከ 2006) ባሉት አሥራ አምስት ዓመታት ውስጥ

<<113 መዋዕለ ሕፃናት፣ 1598 አንደኛ ደረጃ፣ 64 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ 54 ኮሚኒቲ ኮሌጆች፣ 3 ዩኒቨርስቲዎች መከፈታቸውንና አግልግሎት በመስጠት ላይ

መሆናቸን ያስረዳል። ይህ በክልሉ በግል የተቋቋሙትን 51 የአንደኛ ደረጃና 13 የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ሳይጨምር ነው። በአጠቃላይ በመማር ማስተማር ሂደት ሕዝቡ በነቂስ ተጠቃሚ የሆነ መሆኑን የመንግሥቱ መረጃ እንዲህ ሲል ያጠቃልለዋል። «በአንደኛ ደረጃና በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአዲስ ተመዝጋቢዎች ቁጥር በ482 ነጥብ 6 ፐርሰንት አድጓል ይላል። በዚህ ተጠቃሚው ጥቂቶች ወይስ ብዙኃኑ?" (ምንጭ ጌታቸው ረዳ ኢትዮጵያን ሰማይ ድረገጽ አዘጋጅ 2006 ፈረንጅ አቆጣጠር ወደ አማርኛ ተተርጉሞ የቀረበ)>>

ሌሎች አስፈላጊ ተቋማት ለመዘርዘር ብንሞክር መጽሐፍ አይበቃም። ሌሎች አካባቢዎች አይኑን ያተኮረው ከምርጫ 67 በኋላ ነው። አይደለም እንዴ? የሚከደኝ ሰው ያለ አይመስለኝም!

ለምሳሌ ፕሮፌሰሩ "የተሻለ ጤና፤የተሻለ ትምህርት አላገኘም" ብለው በድፍን ከመከራከር ባሻገር፤ ትግሬዎች በድህነት እየማቀቁ ለመሆናቸው የሚሰጡን መከራከሪያ ካንድ ምሁር የማይጠበቅ ማስረጃ ይሰጡናል። የተሻለ ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ባይገባኝም፤ ከድሮ ወይስ ከተቀሩት አካባቢዎች? የሚለው እጠይቃለሁ። ሁሉም አያስኬዱም።

ይህ መከራከሪያው ደግሞ፤

<<ወያኔ ትግራይን ከተቆጣጠረ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ የትግራይ ሕዝብ በአጠቃላይ ያገኘውን ጥቅምና የኑሮ መሻሻል — እያንዳንዱ አባወራ ራሱንና ቤተሰቡን በየዕለቱ በተሻለ ሁኔታ መመገብ፣ ማልበስ፣ የተሻለ መኖሪያ ቤት፣ የተሻለ የጤና አጠባበቅና ትምህርት … አግኝቷል ወይ?>>(መስፍን ወ/ማርያም የወቅቱ ትንተና ጽሁፍ የተገኘ)። መልሱ በተገነቡት ተቋማት (ሆስፒታል፤ትምሕርት፤ትራንስፖረት..) አዎ ሁሉም በሚያሰኝ መልኩ ይገለገላል። ፤ ባማካይ መለኪዩ ግን የትግራይ ማሕበረሰብ ድሮ ከነበረው ሁሉ እያንዳንዱ ቤት ባይሆንም ባብዛኛው ራዲዮን ወይንም ቴ/ቪዥን እና የጸዳ ሳሎን፤ ሞባይል ስልክ አለው። በገጠሬው (አብዛኛው የቆርቆሮ ክዳን ቤቶች በገፍ ተሰርተዋል፤ መብራት በሁሉም ገጠር እና ከተማ በሚበል መልኩ፤ከሌሎች ክ/ሃገሮች ሲነጻጸር)።

የሚገርመው ጥያቄ ግን እንዴት እያንዳንዱ አባወራ በየዕለቱ በተሻለ ሁኔታ መመገብ፤ማልበስ፤የተሻለ መኖርያ ቤት፤የተሻለ የጤና አጠባበቅ ትምህርት.........አግኝቷል ወይ? ተብሎ ይጠየቃል? በዓለም ታሪክ ውስጥ በማንም ሃብታም የተባሉ አገሮች ውስጥ እያንዳንዱ አባወራ ራሱን እና ቤተሰቡን በፕሮፌሰሩ እንደሚጠየቀው ጥያቄ ያሟላ አገር በታሪክ የለም። ድሆች ሃብታሞች፤ጭራሽ መናጢዎች በሚል የምጣኔ ሃብት ትንታኔ ነው የሚገመገመው። ወያኔዎች እንኳ በውስጣቸው የተለያዩ ኑሮዎች የሚኖሩ ናቸው። ሁሉም እያንዳንዱ ወያኔ እንዳልነበረ ሁሉ፤ እያንዳንዱ ጀርምን ናዚ እንዳልነበረ ሁሉ፤ ሁሉም አብሮ አይሞትም፤ ሁሉም አብሮ አይጠግብም፤አይጠቀምም፤......በግምገማ ግን 'ለዓይን የሚታይ' ተብሎ ነው የሚተነተነው። የፕሮፌሰር *1 ትግሬ ሃብታም ከሆነ ሺህ ትግሬ ድሃ ነው* ላሉት

መልስ ፕሮፌሰሩ እንዲህ ሲሉ አዲስ አባባ ነው የሚኖሩት፡ ታዲያ እነ ጓል መቀሌ እና ለማኙ ቄስ ባሉባት ከተማ” አዲስ አባባ የሚኖሩ አንድ ወዳጄ የሚነግሩን ግን ከፕሮፌሰሩ የተለየ ነው። እንዲህ ይላሉ

<<አዲስ አበባ ውስጥ ከመቶ ዘመናዊ የግል አውቶሞቢሎች ለወያኔዎች በሚያዳላ አነስተኛ ግምት ስልሣው የትግሬ ነው፡፡ አዲስ አበባ ውስጥ ከሚታዩ መቶ ታላላቅ የግንባታ ሥራዎች መካከል ባመዛኙ መቶኛ የትግሬ ናቸው– ለምን እንዋሻለን? ከትግሬዎች ጋር ምንም ዓይነት ውድድር የለም፤ እነሱ ሁሉ በጃቸው ሁሉ በደጃቸው ነው – የማውቃት አዲስ አበባ ወዴት ሄደች ብለህ ብትጠይቅ መልሱ በመቀሌ ተዋጠች ነው – መቀሌን ሆነች” (ምህረት ዘገየ፡- አትዮ-ሰማይ ድረገጽ የተለጠፈ መጣጥፍ) >>(ምንጭ ጌታቸው ረዳ የትግሬ ብሔረተኞች መጽሐፍ።)>>

ባንድ “ቪለጅ ክላስተር” ባንድ የገጠር ስብስብ እንኳ ስንመለከት የተለያየ የኑሮ እርከን ውስጥ ይገኛሉ፤ ወንድ ላጤ እና 4 ልጆች ያሉት ወዘተ.....የሚታየው ኑሮ ዝርዝር ውስጥ ከተገባ ፍጹም ይለያያል። ሆኖም በድሃ ገጠሮች ውስጥ ድሃ ተብሎ ሲወሰን ለዓይን የሚታይ ድህንት የተጋለጠ ማለት አንጂ በገጠሩ ውስጥ እያንዳንዱ አባዎራ የተለያ ኑሮ አላቸው family level poverty የሚባለው የድህነት/ኑሮ ደረጃ አንድ ሊሆን ከቶ ኣይችልም (1) the rich having an abundance of means of production/ 2-middle class/3-subsistence producers having some access to income and assets/4) the very poor having very little access/ 5) the destitutes including the handicapped: those who are not able for whatever reason to help themselves) የመሳሰሉ ስንመለክት ሁሉም ባንድ እርከን እና የኑሮ ደረጃ አንደማይኖሩ ሁሉ፤ አንድ ስርዓትም “ሁሉም” በሚያስብል “እያንዳንዱ አባ ቦራ” እኩል አይጠቀምም።

አልተጠቀሙም በሚባሉት (ከጠቀሜታው የተገለሉት የሚባሉት) እንኳ ሁሉም እኩል አይደሉም። የየራሳቸው ምደባ አላቸው፡- ሊቃውንቱ የሚነግሩን ለምሳሌ፤- The disadvantaged people are classified as follows:በሚለው ሲተነትኑት፤- 1) the marginally poor (small farmers), 2) the poor (small farmers-part-time labourers), 3) the very poor (labourers and part-time micro farmer-labourers) and 4) the destitutes (those without an economic base). ስለዚህ ፕሮፌሰሩ እንደሚሉት “ሁሉም” “እያንዳንዱ አባ ወራ” የሚባል አማራኛ እየተጠቀሙ ለክርክሩ ደንቃራ የሆነ መንገድ ይዘው መከራከር ከትንተና እና ተፈጥሮ ሕግ ውጭ ነው።

% ፐርሰንት ኦፍ ፐር ካፒታል የሚባለው የምጣኔ ሃብት መለኪያ ሰንጠረዥ ስንመለከት ከሕዝቡ ብዛት እና አነስተኛ ሰንጠረዥ ከሌሎቹ ሲነጻጸር በድህነት ወይንም ፕሮፌሰሩ

እንደሚሉት “በልመና” ወይንም ‘በቆሼ’ ወይንም እንደ ሶማሌው ወይንም እንደ ወሎው፤ የተራበ ገጠር የሚኖር አይደለም (በአካባቢውደረቅ ሲኖር ተሎ ይቆጣጠረዋል። ትግራይ እንደ ድሮው በረሃብ የሚሞት በገፍ የሚታይ ሕዝብ የለም)። ለምሳሌ ልጆቿ በረሃን የተነጠቀቺው ‘ሃዋ’ ን ልብ ይለዋል (ወያኔው ካድሬ ቢኒያም ኢትዮጵያ ፈርስት ሄዶ አስፈራርቶ ረሃብተኞቹ ለገለልተኞች ጋዜጠኞች የሰጡትን ቃል እንዲያስተባብሉ ያደረገውን አስታውሱ)። ያውም ለሶማሌውም ለሌላውም ከገነባው የእሕል ጎተራው እና ካከማቸው ገንዘብ አውጥቶ መንግሥትን በማበደር ለሌለቹ አከፋፋይ የሆነበት አካባቢ ነው (ይህ ድርጅት እኮ ለጤና ጥበቃ የመድሃኒት ግዢ ያበደረ ነው። ትግራይ ውስጥ የመድሃኒት ቅርበት ከሌሎቹ በተሻለ መኖሩን አትዘንጉ) ። ሃብታሙ የወያኔ ነው፤ኤፈርት ነው ምንትስ የምትለው ቃል በቂ መከራከሪያ ሆና አላገኘናትም። ኤፈርት፤ ከሌሎቹ ይልቅ ለትግሬዎች በብዙ መልኩ ጠቅሟል። ዘመዶቼ የራሴ ወንድሞች እና እህቶች በወያኔ አልተጠቀሙም (የድርጅቱ ታጋዮች ቢኖሩም)፡ አንደኛው ወንድሜ እማ እስካሁን ድረስ ጥይት እራሱ ላይ ገብታ እስካሁን ድረሰ አለች። በበሽታ ሲሰቃይ ዞር ብለው አላዩትም። ግን፤ ግን፤ግን...አብዛኛዎቹ የተጠቀሙ ናቸው።ወያኔ ሲገባ (በነ ገብሩ አስራት ዘመን) በሦስት አመት ውስጥ 13 ፕሮጄክት ሲመሰርት፤ በኦሮሞ እና ደቡብ እንዲሁም ምስራቅ (ሐረርጌ) አማራ ማሕበረሰብ ከነ ነብሱ ሲገፈተር ነበር (ፕሮፌሰሩ ከኔ በላይ ይህንን ያውቃሉ)፡አማራ ህጻናት ተለይተው ከነ ነብሰቻው ትምህርት ገበታ እንዳሉ መዝግያ ተዘግቶባቸው ተቃጥለዋል። ሰሞኑን የወልቃይት ተወላጅ “ቴዎድሮስ ትርፌ” የተባለ ወንድማችን “ኮንገረሺናል ሂሪንግ” በሚባለው የአሜሪካ “ፓርላማ” አባሎች በተሰበሰቡበት የሚቀርብ ሕዝባዊ አቤቱታ ቀርቦ “አንዲት አማራ እናት ተገድላ ልጅትዋ የእናትዋን ደም እንድትጠጣ ተደርጓል” ሲል ምስክርነቱን ሲገልጽ አሜሪካኖቹ “በድንጋጤ“አው!” ሲሉ ድምጻቸው ሰምተናል።

ሁለት ልትረስዋቸው የማይገቡ መቀሌን ከጎበኘ አንድ እውቅ ጋዜጠኛ እና ከመለስ ዜናዊ ንግግር ሁለት ጠቃሚ ማስረጃዎችን ልጥቀስ እና ልደምድም። የመጨረሻው የመለስ ንግግር የትግራይ ሕዝብ ካልተጠቀመ ህወሓት ምን እንደሚገጥመው ስለሚያውቅ ያንን፤ “ማመጣጠን” ስላላበት ህወሓት ትግራይን አልጠቀመም ለሚሉ ሁለት ማስረጃዎች ልጥቀስ።

(1)

<<.....ሆኖም መቀሌ በገዢው ፓርቲ ደስተኛ አትሁን እንጂ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ልቧን ከፍታ የሰጠችም፤የምትሰጥም አትመስልም። በሐገሬው ዘንድ በህወሓት መጨከን በወለዱት መጨከን ተደርጎ ይታያል። ብዙ ታሪካዊ ምክንያቶች ሕዝቡ እንዲያ እንዲሆን አስችለውታል። የህወሓት እና የትግራይ ባንዴራ አንድ ናቸው። ከኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር መሳ የህወሓት መዝሙር በትምህርት ቤቶች ይዘመራል።>> “በኤርትራ ሙዚቃ የምትደንስ ከተማ” ማሕሙድ ሰልማን/ የአዲስ ነገር ጋዜጠኛ” ሰረዝ የተጨመረ (የትግራይ ብሔረተኞች ..በሚለው መጽሐፍ የተጠቀሰ ደራስ ጌታቸው ረዳ ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ )

የወያኔ የጎሳ አመሰራረት አነሳሱ ትግራይን ለማሳደግ እንደሆነ የድርጅቱ ፖለቲካዊ ጻባይ ምሁራን እንዴት ሊስቱት እንደቻሉ ግራ ይገባኛል። ከድርጅቱ መሪ መለስ ዜናዊ  በራሱ በወያኔ ፓርላማ ከነ ቡልቻ ደመቅሳ እና ተመስገን ዘውዴ ሲከራከር የተናገረውን የማያወላዳ ማስረጃ ላቅርብ እና ልደምድም።

(2)

<ከየትኛውም የደረግ ዘመቻ በላይ ሊያጠፋን የሚችል ርሃብ እንደሆነ ነው ያወቅነው። ከየትኛውም ወታደር፤ከየትኛውም አይሮፕላን ታንክ ደርግ ኩሉም በላይ እንደ ድርጅት ሊያጠፋን የሚችል ርሃብ መሆኑን አውቀናል። እንዳለ ነው ድርጅቱ በ77 ዓ.ም የሚሸሸው። ይሄ ነገር ከቀጠለ ያለ ምንም ጥርጥር ህልውናው እንደሚያከትም አንዳችንም አልተጠራጠርንም። ስለዚህ ደርግ ያን ጊዜ 'ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግምባር' ነበር የሚለው፡ ህወሓት የያዘው መፈክር ደግሞ "ሁሉም ነገር ሕዝብ እንዳይራብ" የሚል መፈክር ነበር። ሕዝብ ከተራበ እንደሚሞት ህወሓት ያውቃል። ተማሪ ሆነን የተነገረን ተረት የሚያስታውሰኝ፤< አንድ አባይ ጠንቋዮችን የሚጠላ ንጉሥ ነበር ይባላል።አንድ አባይ ጠንቋይ ወደ አካባቢው ብቅ ሲል ንጉሡ ያየዋል።ንጉሡም ይዛችሁ አምጡልኝ እገርፈዋለሁ ብሎ ያስመጠዋል። አንተ ጠንቋይ ነህ? ይለዋል "አዎ"፤ ታውቃለህ ለወደፊቱ የሚሆነውን ነገር? ይለዋል፡ "አዎ ንጉሥ ሆይ" ይለዋል። አንግዳውስ የምታወቅ ከሆንክ "እኔ መች እንደምሞት ንገረኝ" ብሎ ጠየቀው። ጠንቋዩም ብልጥ ነበርና "እኔ ከሞትኩኝ በማግሥቱ" ብሎ ነገረው። በዚህ ጊዜ ንጉሡ ይህ ጠንቋይ አባይ ጠንቋይ ነው ብለው ባብዛኛው ቢያምኑም፤ ግን አደጋ አለው። እሱ በሞተ በማግስቱ እኔም የምሞት ከሆነ፤ ይህንን አደጋ ከምሸከም ይኼን አባይ ጠንቋይ ተሸክሜ ብኖር ይሻለኛል ብለው እየቀለቡት ኖሩ ይባላል። ህወሓትም እንደ ንጉሡ የሚያውቀው ነገር ነበር።የትግራይ ሕዝብ በረሃብ ባለቀ በነጋታው ህወሓት ይሞታል።በነጋታው! ስለዚህ እንደ ንጉሡ ቢወድም ባይወድም፤ብያምንበትም ባያምንበትም ፤የትግራይ ሕዝብ በረሃብ እንዳያልቅ መከላከል ነበረበረት።ምክንያቱም 'የትግራይ ሕዝብ በረሃብ ባለቀ በማግስቱ ህወሓት እንደሚሞት ስለሚያውቅ።የጠንቋይ ጉዳይ አይደለም። ምክንያቱም በተግባር በ77 በተግባር አይቶታል።ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ እስከምን ርቀት ድረስ ሄዷል። በሂደት ከሱዳን ምግብ ዕርዳታ በብዛት ይመጣ ጀመር፤ይህንን የሚያንቀሳቅስ መዋቅር እና መኪኖች በዕርዳታ ተገዙ።ይህ ግን በቂ አልነበረም። ሕዝባችን አይሮፕላን እንዳይጨፈጭፋቸው ሌሊት፤ሌሊት ነበር የሚጓዙት።የነበሩት መኪኖች ቁጥር ከርሃብተኛው ብዛት ለማጓጓዝ አነስተኛ ነው። ስለዚህ በቂ አይደለም፤ ስለዚህ ወቅቱ ከደርግ ጋር ጦርነት በጦፈበት ወቅት ስለነበር ይህንን ሕዝብ ለማዳን ከደርግ ጋር በመደራደር እህል ለተራበው ሕዝብ እንዲደርስ አንድ የመኪና ቀጠና መንገድ ከደርግ እና ከኛ ከጦርነት ነጻ ቀጠና እንዲሆን ተደራደርን። ከደሴ ጀምሮ እስከ አዲግራት በኩል የሚያልፈው የመኪና መንገድ እኛም ዝር እንዳንል ደረግም ዝር እንዳይል ተፈራርመን 'በዚች' መስመር ካዲስ አበባ፤ደሴ ወደ መቀሌ እና አዲግራት እህል ተጭኖ

መንግሥታዊ ባልሆኑ ድረጅቶች እንዲካሄድ ባመድረግ ሕዝባችን እሕል እንዲያገኝ በማድረግ፤ ከደርግ ጋር ለዚህ ዓላማ ስንል ተደራድረናል። በሌላ ጉዳይ ከደርግ ጋር ተደራድረን ተስማምተን ያደረግነው አንድም ነገር የለም።በምግብ ዕርዳታ ግን የምግብ እና _የመኖር ሕለውና_ ጉዳይ ስለሆነ ተደራድረናል። በዚህ በቁጥጥራችን አካባቢ ባለው በመሬታችን መሃል፤ለማሃል ሰንጥቆ የሚያልፉ መኪኖች አንነካም፤ 'ብቻ እህል' አመላልሱበት፤ምንም ዓይነት አደጋ እንዳይደርስ እንቆጣጠራለን፡በዚህ አካባቢ ምንም አይነት ውግያ አናካሂድም ብለን ተስማምተን ቃል ገብተን መንግሥታዊ ያልሆኑ መኪኖች እህል እንዲያጓጉዙበት ተፈራርመናል። ህወሓት የሰራው ስራ ሕብረተሰቡን ማስራብ ሳይሆን ባለው አቅም ሁሉ፤መመገብ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት 'ህዋሐት ለሕብረተሰቡ ታማኝ ስለሆነ ብቻ አይደለም፡ ይህ የሆነበት ምክንያት _ህወሓትም ልክ እንደ ንጉሡ የትግራይ ሕዝብ በርሃብ ያለቀ ዕለት በነገታው እንደሚሞት እርግጠኛ_ ስለነበረ ነው።">> ምንጭ መለስ ፓርላማ ንግግር "የትግራይ ብሔረተኞች.. ደራሲ ጌታቸው ረዳ የተገኘ ጥቅስ" ) ሲል መለስ ዜናዊ በፓርላማው ንግግሩ የትግራይ ሕዝብ እና ህወሓት የተመሰረተው ግንኙነት በምን በምን እንደሆነ ግልጽ አድረጎልናል። ስለዚህ የትግራይን ሕዝብ የገባባትን ቃል ኪዳን እና የተከተለው የጎሳ ፖለቲካ ጸባይ ትግራይን ካልጠቀመ በማግሥቱ ህወሃት እንደሚያከትም ስላሚያውቅ በ27 አመት ውስጥ "ትግሬዎች እንደጠበቅነው አልተንበሸበሸንም፤ ይጨመርልን" ከማለት በስተቀር "ከሌሎቹ በተሻለ አልተጠቀሙም ማለት አይቻልም። ምክንያቱም ካልጠቀመው ድርጅቱ እንዴት በማግስቱ እንደሚከስም መለስ ዜናዊ በግልጽ ነግሮናል።

ከዚህ አኳያ ፕሮፌሮም ሆኑ ሌሎች ሰዎች ከዚህ ንግግር እና እውነታ ምን አንደሚማሩ አቅርቤአለሁ። እውነታው የመቀበል እና ያለመቀበል የናንተው ፋንታ ይሆናል። ጨርሻለሁ። አሁን ካለንበት አረንቋ እንዴት አንውጣ የሚለው በሰጠሁዋቸው ቃለ መጠይቆች ሌላ ተጨማሪ ይህንን ጠቃሚ ፈለግም እንድታዩት እጋብዛለሁ። መፍትሔው ቢረዳ ይህንን ውይይት ያድም ።

**አማራና ኦሮሞ አንድነት ጉባኤ አዲስ የሚገርም ቪዲዮ ተለቀቀ**

https://youtu.be/1szs9dKVZiU

አመሰግናለሁ ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ) getachre@aol.com